መልእክት ሰባት

**ያሕዌን፣ ዘላለማዊውን አምላክ**
**በአፍቃሪ-ደግነቱ፣ በርኅራኄው እና በታማኝነቱ ማወቅ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 2፡19፤ 10፡10፤ 11፡20፤ 20፡12፤ ሰቆ. 3፡22-25፤ 5፡19

**I. ኤርምያስ እግዚአብሔርን በተደጋጋሚ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ብሎ ጠራው—ኤር. 2፡19፤ 5፡14፤ 6፡9፤ 7፡21፤ 9፡7፣ 15፣ 17፤ 11፡17፤ 20፡12፦**

ሀ. "እግዚአብሔር [ያሕዌ] ግን እውነተኛ አምላክ ነው፤ እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው"—10፡10።

1. *ያሕዌ* ማለት "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" ማለት ነው፣ ይህም የሚያመለክተው ያሕዌ ዘላለማዊው፣ ከጥንት የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ እና ለወደፊትም ለዘላለም የሚኖር መሆኑን ነው—ዘጸ. 3፡14፤ ራእ. 1፡4፦

   ሀ. ያሕዌ በራሱ የሚኖር እና ለዘላለም የሚኖር አምላክ ነው፤ እርሱ ጅማሬና ፍጻሜ ሳይኖረው ለዘላለም ይኖራል—ዘጸ. 3፡14።

   ለ. *እኔ ነኝ* የሚያመለክተው ማንነቱ ከራሱ ውጭ በምንም ነገር ላይ የማይደገፈውን እርሱን ነው—ዮሐ. 8፡24፣ 28፣ 58።

2. እኔ ነኝ የሆነው ያሕዌ ብቻ ነው፣ እኛ ደግሞ እርሱ እንደሆነ ማመን አለብን—ዕብ. 11፡6።

3. እንደ እኔ ነኝ፣ ያሕዌ ሁሉን-ያካተተው ማንነት፣ የእያንዳንዱ አዎንታዊ ነገር እና ሕዝቡ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ እውነታ ነው—ዮሐ. 6፡35፤ 8፡12፤ 10፡14፤ 11፡25፤ 14፡6።

4. ከያሕዌ ውጭ ሌላው ነገር ሁሉ ምንም ነው፤ እኔ ነኝ የሆነው፣ የመሆን እውነታ ያለው እርሱ ብቻ ነው—ዕብ. 11፡6።

ለ. "ኩላሊትንና ልብን የምትፈትን በቅንም የምትፈርድ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ"—ኤር. 11፡20፦

1. *የሠራዊት ጌታ* የሚለው ስያሜ ያሕዌ አምላክ ሁሉን ቻይ፣ የሰማያት ሠራዊት ሁሉ ጌታ፣ የሠራዊት ሁሉ አዛዥ እንደሆነ ያመለክታል—20፡12፤ 30፡8፤ 48፡1፤ 50፡18፤ 1ነገ. 22፡19።

2. የሠራዊት ጌታ የክብር ንጉሥ፣ ብርቱው እና ኃያሉ ነው፤ እርሱ የሠራዊቶች አምላክ ነው—መዝ. 24፡8፤ 10።

3. የክብር ንጉሥ፣ የሠራዊት ጌታ፣ በአሸናፊውና በሚመጣው ክርስቶስ አካል የለበሰው የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ነው።

4. *ሥጋ* እንደለበሰው፣ እንደተሰቀለው እና ከሞት እንደተነሣው ክርስቶስ የክብር ንጉሥ ምድርን ለመውረስ እና መንግሥቱ አድርጎ ለመውሰድ ይመጣል፦

   ሀ. የሠራዊት ጌታ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ጦርነት ይሽራል፤ እርሱ በአሕዛብ መካከል ከፍ ከፍ ይላል፣ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ ይላል—46፡9-10።

   ለ. የሠራዊት ጌታ በአሕዛብ ሁሉ ላይ ለመግዛት ሥልጣን አለው፣ እጁም ነገሥታትን ለመሻርና ለማስነሣት ሥልጣን ይዛለች—ዳን. 2፡21።

5. ክህንነት በዘቀጠበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ስሙን "የሠራዊት ጌታ" ብሎ ገለጠ፣ ይህም የሚያመለክተው አስተዳደሩ እንዲህ በዘቀጠ ሁኔታ ላይ በነበረበት ጊዜ፣ የመንግሥቱን አገዛዝ ያመጣ ዘንድ በመላው ሁኔታ ላይ ለመግዛት እንደሚመጣ ነው—1ሳሙ. 1፡3።

**II. "አቤቱ፣ አንተ ለዘላለም ትኖራለህ፤ ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው"—ሰቆ. 5፡19፦**

ሀ. በቁጥር 19 ኤርምያስ ስፍራውን እንዲሁም የእይታውን አቅጣጫ ከራሱ ወደ እግዚአብሔር መለወጡ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ማንነት እና የማይለወጥ አገዛዝ ያመለክታል።

ለ. ኢየሩሳሌም ተገልብጣ ነበር፣ መቅደሱ ተቃጥሎ ነበር፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ሕዝብ በግዞት ተወስደው ነበር፣ ነገር ግን ያሕዌ የአጽናፍ-ዓለሙ ጌታ አስተዳደሩን ለመቀጠል ይኖራል።

ሐ. *አቤቱ፣ አንተ ለዘላለም ትኖራለህ* የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነ እና በእርሱ ዘንድ መለወጥ እንደሌለ ያመለክታል—ቁ. 19፦

1. እግዚአብሔር በከባቢ ሁኔታዎች እና በክስተቶች አይለወጥም፣ የማይለወጥ ሆኖ ይኖራል—መዝ. 90፡2፤ ሮሜ 16፡25-26።

2. በሰው ክልል ውስጥ በእያንዳንዱ መንገድ ለውጦች ይከናወናሉ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ማንነት በተመለከተ ምንም አይነት መለወጥ የለም፤ እርሱ ያው ሆኖ ለዘላለም ይኖራል።

3. አብርሃም “የዘላለሙን አምላክ የእግዚአብሔርን ስም ጠራ”—ዘፍ. 21፡33፡-
   ሀ. በዕብራይስጥ *ዘላለማዊው አምላክ ኤል ኦላም* ነው፤ *ኤል* ማለት *“ሁሉን ቻዩ”* ማለት ነው፣ *ኦላም* ደግሞ *“ዘላለማዊ”* ወይም *“ዘላለም”* ማለት ሲሆን፣ የመጣውም “መደበቅ” ወይም “መሰወር” ከሚለው የዕብራይስጥ ስርወ-ቃል ነው።
   ለ. *ኤል ኦላም* የሚለው መለኮታዊ ስያሜ ዘላለማዊ ሕይወትን ያመለክታል—ተዛ. ዮሐ. 1፡1፣ 4።
   ሐ. አብርሃም ያሕዌን፣ ዘላለማዊውን እና ሁሉን ቻዩን ማንነት፣ በመጥራት ሁሌ እንደሚኖረው፣ ምሥጢር እንደሆነው፣ እንደ ምሥጢራዊው ማንነት፣ ዘላለማዊው ሕይወት የሆነውን እግዚአብሔርን ተለማመደ።

መ. *ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው* የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እና የማይለወጥ አገዛዝ ያመለክታል—ሰቆ. 5፡19፤ መዝ. 45፡6፤ 93፡2፤ ራእ. 4፡2-3፡-
1. የእግዚአብሔር ዙፋን መጀመሪያም መጨረሻም የለውም፤ ዙፋኑ ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል።
2. በሰቆቃወ ኤርምያስ መጨረሻ ላይ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ማንነት እና የማይለወጥ አገዛዝ የሚመለከተው የኤርምያስ ጽሑፍ በእርግጠኝነት መለኮታዊ ነው፡-
   ሀ. የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ማንነት እና ዙፋኑን የሚመለከተው የኤርምያስ ቃል፣ ኤርምያስ ሰቆቃወ ኤርምያስን ሲጽፍ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ እንደነካ ጠንካራ ምልክት ነው።
   ለ. ከሰብዓዊ ስሜቶቹ ወጣ፣ የእግዚአብሔርን ማንነት እና የእግዚአብሔርን ዙፋን ነካ፣ ወደ የእግዚአብሔር መለኮትነት ውስጥም ገባ።

ሠ. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር በማንነቱ እንደ ዘላለማዊው ንጉሥ፣ እንዲሁም በአገዛዙ እንደ ዘላለማዊው፣ የማይናወጠው መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ይገለጣል፤ ማንነቱና አገዛዙ ከሕዝቡ ጋር ላለው ልውውጥ የማይናወጡ መሠረቶች ናቸው—ዕብ. 12፡28፤ ራእ. 22፡3።

## III. “ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና። ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህ ብዙ ነው”—ሰቆ. 3፡22-23፡-

ሀ. ያሕዌ “በቸርነት ሳብሁሽ” ብሎ በመናገር ለኤርምያስ ተገለጠለት—ኤር 31፡3፡-
1. የያሕዌ አፍቃሪ-ቸርነቱ ውድ፣ ዘላለማዊ እና ከሰማያት በላይ ከፍ ያለ ነው እንዲሁም ለእግዚአብሔር ግንባታ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ወደሆነው ክርስቶስ ይመራል—መዝ. 36፡7፣ 9-10፤ 108፡4፤ 118፡1-4፣ 22-29፤ 136፡1፣ 26።
2. ኃጢአቶችን ይቅር በማለቱ፣ በመፈወሱ፣ በመዋጀቱ እና ሕዝቡን በመንከባከቡ መዝሙር 103 በአፍቃሪ-ቸርነቱ እና በርኅራኄው ስለ እግዚአብሔር ታሪክ ይናገራል።
3. ዘማሪው ያሕዌን “እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ” አለው—5፡7፡-
   ሀ. በጽዮን ተራራ ላይ ወደነበረው መቅደስ የመግባት እድል የነበረው ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር አፍቃሪ-ቸርነት ሥር መሆን ነበረበት።
   ለ. በእርግጥም፣ ወደ መቅደሱ ውስጥ መግባት ራሱ የእግዚአብሔር አፍቃሪ-ቸርነት መትረፍረፍ ድሰታ ነበር።
   ሐ. በመቅደሱ መካከል የያሕዌን አፍቃሪ-ቸርነት ማሰብ እኛ አፍቃሪ-ቸርነቱን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደምንነካ ያመለክታል።
4. ክርስቶስ በምድር ላይ በአፍቃሪ-ቸርነት እና በፍትህ እንዴት እንደሚነግሥ መዝሙር 101 ይገልጣል።

ለ. የእስራኤል ሕዝብ ወድቀው ነበር፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ርኅራኄ ለኢኮኖሚው መከናወን የእስራኤልን ቅሬታ ጠበቀ—ሰቆ. 3፡22-23፡-
1. ርኅራኄ ከምሕረት ይልቅ ጥልቅ፣ ረቂቅ እና የበለጠገ ነው—ሮሜ 9፡15፤ መዝ. 103፡8።
2. ርኅራኄ ከእግዚአብሔር አፍቃሪ ውስጠ-ነገር የሚመነጨውን የእርሱን ውስጣዊ አፍቃሪነት ያመለክታል—2 ቆሮ. 1፡3፤ ያዕ. 5፡11፤ ሉቃ. 6፡36።
3. ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ምሕረት ከተሞላው ከእግዚአብሔር ርኅራኄ የተነሣ ነበር—1፡78።
4. የያሕዌ ርኅራኄ “ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው”—ሰቆ. 3፡23፡-
   ሀ. እንደ ርኅሩኅ ማንነት ጌታን በየማለዳው ኤርምያስ ይነካው እንደነበር ቁጥር 23 ያመለክታል።
   ለ. ከጌታ ጋር በነበረው ግንኙነት ነበር ኤርምያስ የእግዚአብሔርን አፍቃሪ-ቸርነት፣ ርኅራኄ እና ታማኝነት በተመለከተ ቃል የተቀበለው።

ሐ. ኤርምያስ ያሕዌን “ታማኝነትህ ብዙ ነው” አለው—ቁ. 23፡-

1. የእግዚአብሔር ርኅራኄ አይከሽፍም፣ ምክንያቱም እርሱ ታማኙ ነውና—መዝ. 57፥10።
2. እግዚአብሔር ለገዛ ቃሉ ታማኝ ነው፤ ራሱን ሊክድ አይችልም፤ ባሕሪውንና ማንነቱን ሊክድ አይችልም—2 ጢሞ. 2፥13።
3. በታማኝነቱ እግዚአብሔር ወደ ልጁ ኅብረት ውስጥ ጠርቶናል፣ እንዲሁም በታማኝነቱ በዚህ ተሳትፎ እና ድሰታ ውስጥ ይጠብቀናል—1 ቆሮ. 1፥9።
4. የጠራን ታማኙ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ይቀድሰናል እንዲሁም ሁለንተናችንን ፈጽሞ ይጠብቃል—1 ተሰ. 5፥23-24።

## IV. "ነፍሴ፦ እግዚአብሔር እድል ፈንታዬ ነው፤ ስለዚህ ተስፋ አደርገዋለሁ አለች"—ሰቆ. 3፥24፦

ሀ. ያሕዌ እድል ፈንታችን ስለመሆኑ እና እኛ በእርሱ ተስፋ ስለማድረጋችን የሚናገረው የኤርምያስ ቃል የአዲስ ኪዳንን ጣዕም ይዟል—ቆላ. 1፥12፣ 27፦

1. ኤርምያስ ያሕዌን እንደ እድል ፈንታው ተደሰተው፣ እንዲሁም እምነቱን በራሱ ላይ ወይም በምንም ነገር ላይ ሳይሆን በያሕዌ ላይ ብቻ አደረገ—ሰቆ. 3፥24፦
   ሀ. በአንድ በኩል፣ ኤርምያስ እግዚአብሔር የአፍቃሪ-ቸርነት አምላክ እንደሆነ፣ ርኅሩኅ እንደሆነ፣ ቃሉም ታማኝ እንደሆነ ተገነዘበ።
   ለ. በሌላ በኩል፣ በየማለዳው ጌታን መንካት እንደሚያስፈልገን፣ መላው ተስፋችንን በእርሱ ላይ መጣል እንዳለብን፣ እርሱን መጠበቅ እና ስሙን መጥራት እንደሚያስፈልገን ኤርምያስ ተገነዘበ—ቁ. 23-25፣ 55።
2. ዘማሪው ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ሲገባ እና የራሱን ሁኔታ በተመለከተ መለኮታዊ እይታ እና መረዳት ሲያገኝ፣ እግዚአብሔር ለዘላለም እድል ፈንታዬ ነው ማለት ቻለ—መዝ. 73፥17፣ 26፦
   ሀ. በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ ዘማሪው እግዚአብሔርን ራሱን ብቻ እንደ እድል ፈንታው እንዲወስድ፣ ከእግዚአብሔር ውጭ ሌላ ምንም ነገር እንደ እድል ፈንታው እንዳይወስድ ተምሮ ነበር—ቁ. 26።
   ለ. የእርሱን ፈላጊዎች በተመለከተ የእግዚአብሔር ውጥን ሁሉን ነገር በእርሱ ውስጥ እንዲያገኙ እና እርሱን ሙሉ በሙሉ ከመደሰት እንዳይዘናጉ ነው።

ለ. "እግዚአብሔር በተስፋ ለሚጠብቁት ለምትሻውም ነፍስ መልካም ነው"—ሰቆ. 3፥25፦

1. እግዚአብሔር እውነት፣ ሕያው፣ ርኅሩኅ እና ታማኝ ቢሆንም እንኳን፣ ሕዝቡን ይፈትን ዘንድ ቃሉን ለመፈጸም አብዛኛውን ጊዜ ይዘገያል—መዝ. 27፥14፤ 130፥6፤ ኢሳ. 8፥17፤ 30፥18፤ 64፥4።
2. ዘላለማዊውን አምላክ መጠበቅ ማለት ራሳችንን ማስቆም ማለት ነው፤ ይህም ማለት፣ ራሳችንን ከኑሮአችን፣ ከሥራዎቻችን እና ከእንቅስቃሴዎቻችን ጋር ማቆም እና እግዚአብሔርን በክርስቶስ እንደ ሕይወታችን፣ እንደ ማንነታችን እና እንደ ምትካችን መቀበል ማለት ነው—40፥28፣ 31፦
   ሀ. ጌታን የመጠበቅን ትምህርት መማር ያስፈልገናል—30፥18።
   ለ. ዛሬ የከፍተኛው እና የመጨረሻው ድምዳሜ ጊዜ አይደለም፤ ስለዚህ፣ ጌታን መጠበቅ ያስፈልገናል—64፥4።
3. ጌታን ስንጠብቅ ሳለን፣ እርሱን መፈለግ እና እርሱን መጥራት አለብን፦
   ሀ. "እናንተ ትሹኛላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ"—ኤር. 29፥13።
   ለ. "ወደ እኔ ጩኽ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ"—33፥3።

*© 2020 Living Stream Ministry*